# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሓይሎች ሕብረት
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ለዴሞክራሲያዊ ለዉጥ የጋራ ትግል

ዛሬ በዴልፍት ከተማ የ2007 ዓ.ምን የእግር ኳስ ዉድድር ለመሳተፍ ከአዉሮፖ አሕጉር የተሰበሰባችሁ የእግር ኳስ ተጫዋቾች፣ስፖርተኞችና ደጋፊ ዜጎች!!!

በሆላንድ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሐይሎች ሕብረት የድጋፍ ኮሚቴ እንኳን ደሕና መጣችሁ እያለ ልባዊ ሰላምታዉን ያቀርብላችሓል ።

የቅንጅት መሪዎችና የተዎሰኑ የነፃጋዜጤኞች አባላት ከአንድ ዓመት ተኩል እንግልት በሁዋላ ከኢሕአዴግ እስር ቤት በመፈታቸዉ፣የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች፣ የኢትዮጵያን አንድነትንና ልዑላዊነትን፣ ለማስከበር የተስለፋችሁ፣ለዴሞክራሲአዊ ለዉጥ መስወትነትን የከፍላችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ።

በምርጫ 97 የተሸነፈዉ አሸባሪዉና አምባገነኑ ስርዓት የቅንጅትን መሪዎችንና የተዎስኑ የነፃ ጋዜጣ አዘጋጆችን በመፍታቱ በምርጫዉ ማግስት ለፈጸማቸዉ የአፈናና የግድያ ወንጀሎች ከተጠያቂነት እንዳይሸሸግ ድምፁን የተነጠቀዉ  የኢትዮጵያ ሕዝብና የተቋዋሚዉ ሓይሎች ለሚያደርጉት ዘመቻ የዜግነት ግዴታችንን ያለማወላወል በጋራ እንድንወጣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሓይሎች ሕብረት ጥሪዉን ያደርጋል። በመሆኑም የወሳኙ ትግል አቅጣጫ፣

1. ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ዕዉን የሚሆነዉ በነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንጂ ገዢዉ ድርጅ ት በዴሞክራሲ ጎዳና የተከለኩአቸዉን ዉስብስብ መሰናክሎችን አልፋችሁ ስልጣን ተጋሩኝ፣ በኢሕአዴግ ማዕከልነት ለሚረጋገጥ ስልጣንም ተወዳደሩኝ እያለ ተቃዋሚወቹን የሚያስገድድ በትን የአፈናና የማስፈራሪያ ስልቱን ለአንዴና ለመጨረሻዉ  ለማምከን
2. ከዚህ በፊት በተደረጉ ምርጫ ተብዬ ማጭበረበሪያዎችም  ሆነ በምርጫ 97′ የተነጠቀዉን የሕዝብ ድምፅ ለስልጣን ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲመልስ በተባበረ ሓይል ለማስገደድ፤
3. በተቃዋሚዎች መካከል የሚነሱትን ልዩነቶችን የሚመረምርና የመፍትሔ ሐሳብም የሚያቀርብ ሕዝብንና አገርን ያስቀደመ መፈትሔ የሚያፈላልግ የጋራ ኮሚቴ ለመሰየም፤
4. ባዕዳን ሓይሎች ለራሳቸዉ ጥቅም ሲሉ ወያኔ / ኢሕአዴግን በርታ አይዞህ ! ማለታቸዉን እንዲያቆሙና ከወያኔ ስርዓት በሁዋላም ለሌላ በታኝና ከፋፋይ ሓይል አሳልፈዉ ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆናቸዉን  አዉቀን በተባበረና ተከታታይ በሆነ  የዲፒሎማሲ ዘመቻ ለአፋኙ ስርዓት የሚለግሱትን ሁለገብ ርዳታን ለማሰቆም፣
5. የተቃዋሚ ሓይሎች ያነገቡአቸዉ ጥያቄዎችና የፖለትካ መርሐግብሮች ምላሽ እሰክያገኙ ድረስ የጋራ ትግል ወሳኝነት የሚመነጨዉ ባገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመሆኑ፣የኢትዮጵያ ዴሞክራ ሲያዊ ሓይሎች ሕብረት፣ ይህንን አስከፊና አደገኛ ሁኔታን በመገምገም፣ የጋራም መፍትሔ ማፈላ ለግ አማራጭ የሌለዉና የወቅቱ አነገብጋቢ ጥያቄ ነዉ ብሎ በማመን ሁሉን አቀፍ የጋራ ጉባዔ በሁሉም ሰላም ወዳድ ሓይሎች ትብብር እንዲጠራ ያላሰለሰ ጥሪ በማቅረብ ላይ ይገኛል።ከትብብር ዉጪ በምንም መንገድ ይችን አገር ማዳን እንደማይቻል በመገንዘብ፤የተደራጁም ሆኑ ያልተደራጁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ሆነዉ አገር አድን ዕቅድ የሚነድፉበት የጋራ ጉባዔ በጋራ እንዲጠራ ባክብሮት እነጠይቀለን።

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!
የተሰረቀዉ የህዝብ ድምፅ ይመለስ !!!
የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሓይሎች ሕብረት ድጋፍ ኮሚቴ በሆላንድ